የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | |
|---|---|
| 8ኛ ዓመት ቁጥር 14<br>8th Year N° 14 | ሐረር ነሐሴ 15 ቀን 1996 ዓ.ም<br>HARAR . Aug 22th , 2004. |

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ<br>unit price 2.00 | በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሳጥን ቁጥር<br>P.O.BOX 272 |

## ማዉጫ

አዋጅ ቁጥር 45/1996 ዓ.ም
የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1997 የበጀት ዓመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ-----ገጽ 367

## አዋጅ ቁጥር 45/1997 ዓ.ም
## የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1997 የበጀት ዓመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ

በ1997 የበጀት ዓመት በክልሉ ዉስጥ ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገዉን በጀት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ አጽድቆ ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ:

የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ የ1997 በጀት ዓመት በጀት አጠቃሎ ማጽደቅና ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ:

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 2/ሠ መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት/ የማጽደቅና ሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን የተሰጠዉ በመሆኑ ይህ አዋጅ ታዉጇል::

### ክፍል 1
### ጠቅላላ

#### አንቀጽ 1

ይህ አዋጅ የ1997 በጀት ዓመት አዋጅ ቁጥር 45/1997 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

#### አንቀጽ 2

ከሐምሌ 1/1996 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/1997 በሚፈጸመዉ በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ዉስጥ በክልሉ የሚገኘዉ ገቢ እና ከሌላ ገንዘብ ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘዉ ሠንጠረዥ ዉስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ እንደተመለከተዉ:-

ሀ. ለመደበኛ ወጪዎች ብር 57273700
ለ. ለካፒታል ወጪዎች ብር 39316400
ሐ. መጠባበቂያ በጀት ብር 5989900

ድምር ብር 102580000 /አንድ መቶ ሁለት ሚልዮን አምስት መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ ለክልሉ መንግስት ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል::

#### አንቀጽ 3

ለፕሮፌሽናል፣ ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንደዚሁም ለሥራ ማስኬጃ የተፈቀደዉ መደበኛ በጀት ወደ ደመወዝና አበል ማዛወር አይቻልም::

